ለአዲስ ዩኒቨርስቲ ገቢ ተማሪዎች ከቲክቫህ ቤተሰቦች የተሰጠ ምክር

አዲስ ወደ ዩኒቨርስቲ የሚገቡ ተማሪዎች ምን ማድረግ አለባቸው እንዴትስ ማስተካከል ይችላሉ ብለን ከአስተማሪዎችና ከነባር ተማሪዎች ምክር ጠይቀን ነበር። ይህንንም አስመልክቶ በርካታ ቤተሰቦቻችን ምክራቸውን ለግሰውናል እናመሰግናለን። የሁሉንም በአንድ አድርገን አቅርበናል።

1. ፍላጎት፡- መሆን የምትፈልጉትን ነገር መሆን ከፈለጋችሁ ከአከባቢም ሆነ ከሌሎች ፍላጎታችሁ አስበልጣችሁ ፍላጎታችሁን አክብሩ። ለምሳሌ አርክቴክቸር መማር የሚፈልግ ሰው ጓደኞቹን ተከትሎ አሊያም በሌላ ምክንያት አርክቴክቸር የማይሰጥበት ግቢ መሙላት የለበትም። መሙላት ያለበት አርክቴክቸር የሚሰጥበትን ግቢዎች ለይቶ በቅደም ተከተል ነው መሙላት ያለበት። ምክንያቱም ከሁሉም በላይ ፍላጎቱን ማስቀደም አለበት።

2. ውጤት፡- ውጤታችንን የሚመጥን ዩኒቨርስቲ መሙላት ይጠበቅብናል። ለምሳሌ ሜዲስን መግባት ፈልጎ ውጤት ዝቅ ቢልብንና ከተጠራጠርን አዲስ አበባን የመሰሉ ውድድር የሚበዛባቸውን ዩኒቨርስቲዎች ማስቀደም ተገቢ አይደለም። ስለዚህ ከፍላጎታችን ቀጥሎ ነጥቤ የምፈልገውን ፊልድ የሚያስተምረኝ የቱን ባስቀድም ነው ማለት ተገቢ ነው። ይህንን ለማነጻጸር ከፈለጋችሁ ደግሞ በትምህርት ቤታችሁ ከፍተኛው ነጥብ ስንት ነው? ከኔ በላይ ምን ያህል ናቸው? ከኔ በታችስ? እያላችሁ ማነጻጸር ትችላላችሁ::

3. ለፍላጎታቹ ቀረቤታ ያላቸውን ፊልዶች በቅደም ተከተል መሙላት፡- ለምሳሌ አንድ ተማሪ ሜዲስንን አንደኛ ላይ ቢሞላ ቀጣይ ኢንጂነሪንግ ቢሞላ ይህ ልጅ ፍላጎቱን ተከትሎ አልሞላም ማለት ይቻላል። መሙላት የሚጠበቅበት በጤና ዘርፍ ስር የሚመደቡትን ነው።

4. ከአሉባልታ እና ከግፊት ነጻ ሁኑ፡- ምክር ስሙ ነገር ግን የራሳችሁን ችሎታ እና አቅም ፈትሻችሁ በየትኛው የትምህርት ዘርፍ ጠንካራ እንደሆናችሁ አይታችሁ ከዛ በኋላ የመረጣችሁት ፊልድ ከአቅማችሁ እና ፍላጎታችሁ ጋር የሚመጣጠን ከሆነ በሌላ ሰው ተጽዕኖ ሀሳባችሁን አትቀይሩ። ሌላው ደግሞ ስለግቢዎች የሚወሩትንም አሉባልታ አትስሙ እዚህ ግቢ ይከብዳል አይሆናችሁም ይቅር የሚባሉትንም ከአቅማችሁ እና ከችሎታችሁ ጋር አመዛዝኑ እንጂ ፍላጎታችሁን ለሰው አሉባልታ አትቀይሩ። ምክንያቱም ከልባችሁ ከፈለጋችሁ የማታሳኩት ነገር እንደሌለ ማመን አለባችሁ።

5. የት ዩኒቨርስቲ ብገባ ነው ተወዳድሬ የፈለኩት ፊልድ የምገባው፡- በዚህ አመት ፊልድ የምትመርጡት ከአንድ ዓመት ቆይታ በኋላ ስለሆነ የት ብገባ በአቅሜ ተፈኩካሪ መሆን እችላለው የሚለው ታሳቢ ማድረግ ይጠበቅባችኋል። ይህ ማለት ግን ፍራቻን ለመፍጠር አይደለም። ያለንበትን የአቅም ብቃት ማወቅ ለስኬታችን መሰረት ስለሆነ ነው። ውስጣችሁ ግን የትም ቢሆን አሸንፋለው የሚል የጥንካሬ መንፈስ ይዛችሁ ልትጓዙ ያስፈልጋል።

በመጨረሻም፡- ሁል ጊዜ ለአዲስ ነገር ዝግጁ መሆን ይኖርባችኋል። ምንም ቢፈጠር ምንም ከአከባቢ ጋር ከአዳዲስ ጓደኞቻችሁ ጋር፤ ከትምህርቱ ጋር ብቻ ብዙ አዲስ ነገሮች አሁን ወደ ሕይወታችሁ የሚመጡበት ሰዓት ነው። ለዚህም ደግሞ የሕይወት ወንፊት ያስፈልጋችኋል! መልካሙን ከመጥፎው የምትለዩበት ምክንያቱም ይህ ዓመት የሕይወታችሁን መስመር ትወስናለችና ብርታት ጥንካሬ ግድ ነው።

መልካም የትምህርት ዘመን!

TIKVAH-MAGAZINE